# አገስት ዲልማን

## የኢትዮጵያን ጥናት ለዓለም ያሳወቀ ሊቅ

(እ.አ.አ 1823- 1894)

*በእደ ማርያም እጅጉ ረታ*

አንዳንድ ምእመናን ወይም ብዙዎች ለምንድን ነው ወደ ቤተ ክርስቲያን የማትሄዱት ተብለው ሲጠየቁብዙ ጊዜ ደጋግመው የሚሰጡት መልስ ቅዳሴው፣ ማኅሌቱ በግእዝ ስለሆን ስለማይገባን ነው የሚል ሰበብ ነው። በእርግጥ ማኅሌቱ በግእዝ ቢሆንም ቅዳሴው ግን በብዙ አብያተ ክርስቲያናት በአሁኑ ወቅት አብዛኛውን ጊዜ በአማርኛ የሚነበብ ሲሆን በተጨማሪም የቅዳሴ ተሰጥኦ መጽሐፍ ይዞ መከታተል ይቻላል። ማኅሌቱም ቢሆን ዐበይት በዓላት በሚሆኑበት ወቅት በአማርኛም ተተርጉሞ ምእመናን እንዲከታተሉት እየተደረገ ነው። ይሁን እንጂ ምእመናን ይህን ድንቅ የሆነ የያሬድ ዜማ ትርጉሙን ለማወቅ ከቤተ ክርስቲያን በኩል ተዘጋጅቶ ካልተሰጣቸው በስተቀር እምብዛም ራሳቸው ለማወቅ አይጥሩም። በአንጻሩ ደግሞ ምን ያህል ሰዎች የእንግሊዘኛ ወይም የሌላ ቋንቋ ሙዚቃ ገብቷቸው እንደሚሰሙ እርግጠኛ አይደለሁም። በተለይ ግእዝ ለአማርኛ መሠረቱ ስለሆነ ቋንቋው እንዲያድግ በተቻለው ሁሉ ጥረት መደረግ አለበት። በአሁኑ ወቅት የሚታየው የአማርኛ ፊደላትን አለመጠንቀቅ እንዲሁም አንድ ዓይነትድምጽ የሚያወጡትን ፊደላት ለምሳሌ ያህል (ሀ፣ ሐ፣ ኀ፤ ሠ፣ ጸ፣ ዐ) የመሳሰሉትን በአንድ ፊደል ብቻ ለመጠቀም ከማሰብ አልፎ ተርፎ የግእዝ መሠረታዊ ዕውቀት እንኳ የሌላቸው በከፍተኛ የትምህርትተቋም ውስጥ ያሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚሰጡትን አስተያየቶች መስማት አሳፈሪና ግድየለሽነትን ያመለክታል። ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል የአማርኛ ፊደል ይቀነስ የሚል መመሪያ በተወሰኑ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋ ክፍል ኀላፊዎች የወጣውን በመቃወም ለሐመር መጽሔት ከሰጡት ቃለ ምልልስ ላይ የፊደላት ለውጥ ብቻ የቃል ትርጉም ላይ ምን ያህል ልዩነት እንዳለው እንደሚከተለው አስረድተዋል። ለምሳሌ፤ <u>ሀብት</u> የሚል ቃል ወሀበ ከሚለው የመጣ ንብረትን የሚያመለክት ቃል ነው። በሐመሩ ሐ ደግሞ <u>ሐብት</u> ብንለው ሐበበ አመነዘረ ከሚለው ግስ ወጥቶ ፍትወት የሚል ትርጉም ይይዛል። ስለዚህ አንድ ሰው «ሐብት አለኝ» ቢል ንብረት አለኝ ሳይሆን «አመንዝራ ነኝ» ማለቱ ይሆናል ማለት ነው። እንደገና በብዝኃኑ ኀ <u>ኀብት</u> ቢባል ቃሉ ኀበበ ከሚለው ግስ የወጣ ሲሆን፤ ትርጉሙም ወይን ጨመቀ ይሆናል። ስለዚህ አንድ ሰው «ኀብት አለኝ» ቢል ወይን ጭማቂ አለኝ ማለቱ ነው። ከምሳሌው እንደምንረዳው ከረጅም ጊዜ በኋላ ሊከተል የሚችለውን የቋንቋ መፋለስ ካሁኑ መገመት አያዳግትም።

ለምሳሌ በግሪክ ቋንቋ ተመሳሳይ ድምጽ ያላቸው 4 ዓይነት ፊደላት እንዲሁም ሌሎች አሉ። ልክ እንደኛው በግሪክኛም የሚጻፈው ቃል በትክክለኛው ፊደል ካልተጻፈ ትርጉሙ ከመዛባት አልፎ ጸያፍ ነው። ታዲያ ሌሎች እንዲህ ጥንቃቄ ሲያደርጉ የእኛ ግድየለሽነት ምን ይባላል? አሁንም እነዚህ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከግእዝ ቋንቋ ለቃውንት ጋር በመሆን በመተባበር ቋንቋው እንደ ቀደመው ጊዜ ሥርዓቱን ጠብቆ የሚያድግበትን መንገድ መፈለግ በታሪክም ከመወቀስ ያድናል።

የዚህን ቋንቋ ታላቅነት በመገንዘብ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች የውጭ ሀገር ዜጐች ለራሳቸውብቻ ለማወቅ ሳይሆን ከዚያ አልፈው ለሀገራችን የሚጠቅም ትልልቅ ሥራዎችን በግእዝ ቋንቋ ላይ ሠርተው ለትውልድ እየተላለፉ እስከ አሁን እንጠቀምባቸዋለን። ከእነዚህ ታላላቅ ሰዎ

**ች መሐከል ስመ ጥር የሆነው ኦገስት ዲልማን የተባለ ጀርመናዊ ነው። እጅግ ታዋቂ የሆኑት ኢ
ትዮጵያዊው የግእዝ ቋንቋ ሊቅ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ስለዚህ ሰው ታላቅ ሥራ ሲመሰክሩ
እንዲህ ብለዋል፤**
***«ናቀድም ወንኤምር ከመ ዝንቱ መጽሐፍ መዝገበ ቃል ወመጽሔተ ፊደል፣ ግቡር ሐዲስ ወጽሑ
ፍ ስልሰ መጠነ ሰብዐቱ አዝማን፤ ወከመ ለሊሁ ውጹእ ወእስትጉቡእ በኪን እመጽሐፈ ጠቢብ
ዲልማን ወእመጻሕፍት ካልአን እለ ያረትዑ ቃለ ፍኖተ ግእዝ ዘበአማን። እስመ ርቱዓት ፍናዊሁ
ለእግዚአ ልሳን ግእዝ፣ ፍናወ ቃለ ሕግ ወትእዛዝ፤ ጻድቃን የሐውርዎን ወኃጥአን ይስእንዎን በ
ከመ ጽሑፍ (ሆሴ 14፤9)።***

*ዲልማንሰ ሉተራዊ እምነገደ ጌርመን ማእመረ ልሳናት ሴማውያን ወመተርጉመ ግእዝ ኀበ
ላቲን። ጽሩይ ዐይን ወበሊኀ ልሳን፣ ዘርቱአ ይመትር ቃለ መጻሕፍት ወነገረ ኵሉን በሓውርት፤
ወቦ እለ ይብሉ በእንቲአሁ እምደቂቀ ያፌት አርዳኢሁ በለብዎ ወበአንክሮ፣ ዘከመ ወረደ ላእሌ
ሁ መንፈሰ ጥበብ ወአእምሮ፣ ወአስተራትዖሙ በተምህሮ።*

*ወንሕነኒ ዓዲ ኢሰማእነ ወኢርኢነ  ግሙራ፣ ወኢነገሩነ አበዊነ በቃለ ነከራ፣ ከመ ቦ ባእድ እም
ጸዓድው ማእምረ ግእዝ ከማሁ፣ ኢእምቅድሜሁ ወኢእምድኅሬሁ። ዲልማንኬ ድልወ ብጽዓን ወ
ቡራኬ ምስለ አበዊነ በውሳኬ፣ እስመ ሎቱ መጽሐፍ ዘከመ ዝኬ፤ ኅጽዋ ወመጋቢሃ ለልሳነ ግእ
ዝ ህንደኬ፣ ንግስተ ሳባ ወኖባ ወኢትዮጵያ፤ ወግብሩሂ ክሡት ግብረ ሐዋርያ፣ ዘያሜንን ግብጸ ወ
እስክንድርያ። ማእረሩሰለግእዝ ብዙኅ ወፍድፉድ፣ ወገባሩ ኅዳጥ ወውኁድ፤ ሰአልዎ እንከ ኦ አ
ርዳእ፣ ለበዓለ ማእረር እግዚእከመ ይወስክ ካእበ እምድሩ፣ ገባረ ለማእረሩ።*

*ይህንንም ሳእከ ማርያም መጡኑ እንዲህ በማለት ተርጉመውታል « ሉተራዊ የሚሆን ዲልማን ጀ
ርመን ከምትባል ሀገር የሆነ የሴማውያንን ቋንቋ የተማረ በመልካም አንደበት በጥሩ አመለካከት
ግእዝን ወደ ላቲን የሚተረጉም፤ ተሰሚነት ያለው መጻሕፍትን በቀጥታ በእውነት የሚተረጉም፣ የ
ሌሎችንም ቋንቋ የሚያውቅ ከያፌት ወገኖች ስለሱ በአድናቆትና በማስተዋል በላዩ ላይ የመንፈስ
ቅዱስ ጥበብ ከማስተዋል ጋር የተሰጠው ነው ይላሉ። እኛም አባቶቻችን እንደነገሩን እንደዚህ
ዓይነት የውጭ ሰው የግእዝን ቋንቋ ከሱ በፊትም ከሱ በኋላ ሲተረጉም አላየንም። ዲልማን ም
ስጋና ይገባዋል ብለው አባቶች እንዳሉ፣ ግእዝን ለሚያሳምራት እና የሚተረጉማት እሱ ነው፤ ሥ
ራው ግእዝ የህንደኬ ንግሥት ሳባ ቋንቋ በመተርጐሙ ሥራው የሐዋርያት ሥራ ነውና፤ ግብጽን
ወይም እስክንድርያን እንኳ ሥራው የሚያስንቅ ነውና። የግእዝ እርሻው ወይም አዋቂው ብዙ ነ
ው ተናጋሪው ወይም ሠራተኛው ጥቂት ነው። ተማሪዎች(ግእዝ ተናጋሪዎች) ለእርሻው ጌታ ብዙ
ገበሬ እንዲኖር ለመኑት ከእርሻውም መሬት እንዲጨምር ተማጸኑት።»*

**ከዚህ ታላቅ ሰው የምንማረው ቢኖር የማወቅ ፍላጎቱ ካለንና ጥረት ካደረግን ለእኛ ብቻ ማወቅ
ሳይሆንለሌሎችም መትረፍ እንደምንችል ነው። እጅግ ማራኪ የሆኑት የቤተ ክርስቲያናችን ዜማ
ዎች ማለትምየቅዳሴው፣ የማኅሌቱ፣ ሰዓታቱ ትርጉማቸው እየተሰተዋለ፣ እየገባን ስንጸልይ መንፈ
ስን እንደሰከረ ሰውየሚያደነዝዙ፤ ወደ ፍጹም ተመስጦ የሚለውጡ ናቸው። ብዙዎች ቀደምት
አባቶቻችን በታሪክ እንደተጻፈው ለምነና እንደበቁ ልናስተውል ይገባል። ፍጹም ጥረት ካደረግን
ደግሞ የማናውቅበት ምክንያት የለም። ስለዚህ ይህንን የቤተ ክርስቲያናችንን፣ የሀገራችንን ቋንቋ
ልንማረው ልናጠናው ይገባል። ኦገስት ዲልማን አርአያ ቢሆነን በማለት ሚያዚያ** 6 **ቀን** 1979
**ዓ.ም በአዲስ ዘመን ላይ ስለእሱ የሕይወት ታሪክ የወጣውን ከዚህ ቀጥለን እናቀርባለን።**

*« ... ፡ ኢትዮጵያን ፥ በመልክአ ፡ ምድር ፡ እንጂ ፥ ባይኔ ፡ አላየኋትም ። የሀገሩ ፡ አቀማመጥ ፥ የወንዙ ፥ የተራራውና ፡ የሸንተረሩ ፥ በተለይም ፡ ስለ ፡ አየሩ ፡ ተስማሚነት ፡ ሲጻፍ ፡ አነባለኹ ። ቅድመ ፡ ልደተ ፡ ክርስቶስ ፥ ምናልባት ፡ እኛ ፡ በሕንጻ ፡ ኪነ ፡ ጥበብ ፡ ሳንሠለጥን ፥ ኢትዮጵያውያን ፡ ለታሪክ ፡ የሚቈዩ ፡ እጅግ ፡ ተደናቂ ፡ የኾኑ ፡ ሕንጻዎች ፥ ሐውልቶችና ፡ ዋሻዎች ፡ እንዳሏቸው ፡ ለምቻለኹ ። የነማክዳ ፥ የነአዛና ፥ የነያሬድ ፥ የነላሊበላ ፥ የነፋሲል ፥ የነቴዎድሮስ ፡ ምድር ፡ መኾኗን ፡ ዐውቃለኹ ። የቀለም ፡ አያቴም ፥ ሊቁ ፡ አባ ፡ ጎርጎርዮስም ፥ የኢትዮጵያ ፡ ፍሬ ፡ መኾኑን ፡ ተረድቻለኹ ።*

*« ይህቺን ፡ ውብ ፡ የታሪክ ፡ አገር ፡ መጐብኘት ፡ እፈልግ ፡ ነበር ። የዠመርኩት ፡ የሥነ ፡ ጽሕፈት ፡ ምርምርና ፡ ጥናት ፡ ጊዜ ፡ አልሰጠኝ ፡ አለ ። መገናኛውም ፡ እንደ ፡ ልብ ፡ አይደለም ፡ ይሉኛል ። ይኹንና ፥ የኢጣሊያ ፥ የንግሊዝና ፡ የቱርክ ፡ ዜጎች ፥ በቀይ ፡ ባሕር ፡ በኩል ፡ እየደረሱ ፡ ሲመለሱ ፥ የመርከቡ ፡ ጕዞ ፡ ምቹ ፡ መኾኑን ፡ ይናገራሉ ፡ ይባላል ። እኔ ፡ ግን ፥ አልተሳካልኝምና ፥ ያቺን ፡ ድንቅ ፡ የታሪክ ፡ አገር ፡ ሳላይ ፡ የምቀር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ዐፅሜ ፡ ዕረፍት ፡ አያገኝም ። ኾኖም ፥ እኹን ፡ በምሠራው ፡ የግእዝና ፡ ያማርኛ ፡ ጥናት ፥ ስሜ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ ዐልፎ ፡ ዐልፎ ፡ መወሳቱ ፡ አይቀርም ፡ እላለኹ ።»*

ከዚህ ፡ በላይ ፡ በመጠኑ ፡ የተወሳውን ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ ያቀረበልን ፥ በኢትዮጵያ ፡ ጥናትና ፡ ምርምር ፥ በተለይም ፡ በሴማዊ ፡ ልሳን ፡ እጅግ ፡ የተደነቀው ፥ ያ፲፱ኛው ፡ ምእት ፡ ዓመት ፡ ሊቅ ፥ ጀርመናዊው ፡ ክርስቲያን ፥ አውግስጦስ ፡ ዲልማን ፡ ነው ።

ሊቁ ፡ ዲልማን ፥ እ. ፡ አ. ፡ አ. ፡ ባ፲፰፻፳፫ ፡ በምዕራብ ፡ ጀርመን ፥ ኢሊንገን ፡ በተባለ ፡ ከተማ ፡ ተወለደ ። በዚሁ ፡ ከተማ ፥ ያንደኛና ፡ የኹለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርቱን ፡ አጠናቀቀ ። ቀጥሎም ፥ ወደ ፡ ቲዩቢንገን ፡ ኼዶ ፥ መንፈሳዊ ፡ ትምህርትንና ፡ ፍልስፍናን ፡ ተከታተለ ። በዚህ ፡ የሃይማኖትና ፡ የፍልስፍና ፡ ዕውቀቱ ፥ እስከ ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ደርሶ ፥ ስሙ ፡ ሊገን ፡ በቅቷል ።

እ. ፡ አ. ፡ አ. ፡ እስከ፲፰፻፵፭ ፡ ድረስ ፥ የራሱን ፡ ጥናት ፡ በሃይማኖትና ፡ በፍልስፍና ፡ ካጠናቀቀ ፡ በኋላ ፥ በትዩቢንገን ፥ በኪዬልና ፡ በቤርሊን ፡ ከነበሩ ፡ የዘመኑ ፡ ፈላስፎችና ፡ የቀለም ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ተቀምጦ ፥ ሙያውን ፡ አስፋፍቶ ፥ በኹለቱም ፡ ታላላቅ ፡ ሙያዎች ፡ ለመምህርነት ፡ የሚያበቃ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ተቀበለ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፥ ባይነ ፡ ሥጋ ፡ ወዳላያት ፥ ባፍሪቃ ፡ ክፍለ ፡ ዓለም ፥ ምሥራቃዊ ፡ አፍሪቃ ፡ ላይ ፡ የምትገኘውን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ማጥናት ፡ ዠመረ ።

አውግስጦስ ፡ ዲልማን ፥ ታላቁን ፡ የግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ *መጽሐፈ ፡ ግስ* ፥ ወይም ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ [ባ፲፰፻፷፭ ፡ ዓ. ፡ ም.] ፥ በላይፕትዚግ ፡ (ጀርመን) ፡ አሳተመ ።

ምሥራቃውያንንና ፡ የሴም ፡ ቋንቋዎችን ፡ ማጥናትና ፡ መመርመር ፥ እንዲሁም ፡ ማሳተም ፡ ሥራው ፡ አድርጎ ፡ የያዘው ፡ አውግስጦስ ፡ ዲልማን ፥ ከሴማውያም ፡ ኾነ ፡ ከምሥራቃውያን ፡ ቋንቋዎች ፡ መካከል ፡ ቅድሚያ ፡ የሰጠው ፡ ለግእዝ ፡ ቋንቋ ፡ ነበር ። ቀጥሎም ፡ ባማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ላይ ፡ አተኰረበት ።

ኢዮብ ፡ ሉዶልፍ ፡ የተባለው ፡ ሌላው ፡ ጀርመናዊው ፡ ሊቅ ፥ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በዚሁ ፡ ጥናት ፡ ተሰማርቶ ፡ ስለ ፡ ነበር ፥ በትውልድና ፡ ባላማ ፡ አንድ ፡ መኾናቸው ፡ ለዲልማን ፡ በጣም ፡ ረድቶታል ። ሉዶልፍ ፡ *የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ሐተታ ፥ ያማርኛ ፡ ሰዋስውና ፡ የግእዝና ፡ የላቲን ፡ መዝገበ ፡ ቃላት* ፡ በሚል ፡ ርእስ ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ አሳትሞ ፡ ለገበያ ፡ ማቅረቡ ፡ ይታወሳል ። ሉዶልፍ ፡ ይህን ፡ ከፍተኛ ፡ ተግባር ፡ ለመዠመርና ፡ ለማገባደድ ፡ የበቃው ፡ ደግሞ ፥ አባ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ የተባሉ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሊቅ ፥ በዘመነ ፡ ሱስንዮስ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ተሰደው ፥ በመካከለኛው ፡ ምሥራቅና ፡ በኤሮጳ ፡ ባደረጉት ፡ ጕዞ ፥ መዠመሪያ ፡ ሮማ ፡ ከተማ ፥ ቀጥሎ ፡ ጀርመን ፡ ተገናኝተው ፥ የግእዝንና ፡ ያማርኛን ፡ ትምህርት ፡ ስላስጠኑት ፡ ነበር ።

አውግስጦስ ፡ ዲልማን ፥ በየጊዜው ፡ ከኢትዮጵያ ፥ በዘረፋም ፡ ኾነ ፡ በወረራ ፥ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ የተወሰዱትን ፡ መጻሕፍት ፡ ዝርዝር ፡ ተመልክቷል ። በተለይም ፡ ኦክሰን ፡ ከተማ ፡ (የዛሬው ፡ ኦክስፈርድ ፡ ነው) ፡ በሚገኘው ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ ወመዘክር ፥ የሚገኙትን ፡ የኢትዮጵያ ፡ የብራና ፡ መጻሕፍት ፡

ዝርዝር ፡ አውጥቶ ፡ ምስጢራቸውንም ፡ ተረድቶ ፡ ለንባብ ፡ አብቅቷል ።

በኦክስፈርድ ፡ የሚገኙትን ፡ የብራና ፡ መጻሕፍት ፡ ከተመለከተ ፡ በኋላ ፡ ባገኘው ፡ መሠረታዊ ፡ ጥናት ፡ መሠረት ፡ የግእዙ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ከጀርመንኛ ፡ ጋራ ፡ ታተመ ። ከ፺ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ ደግሞ ፡ የግእዙ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ በጀርመንኛ ፡ ብቻ ፡ መኾኑ ፡ ቀርቶ ፡ እንግሊዝኛውም ፡ ተጨመረበትና ፡ ለኅትመት ፡ ቀርቦ ፡ ገበያ ፡ ላይ ፡ ዋለ ።

ባ፳፻፹፮ ፡ ገጾች ፡ ብዛት ፡ በታተመው ፡ ይህ ፡ የግእዝና ፡ የጀርመን ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ዘጠኝ ፡ ታላላቅ ፡ ያገባብና ፡ የቅምር ፡ ሰሌዳዎች ፡ ይገኙበታል ። የግሱ ፡ ርባታም ፡ በነዚህ ፡ ሰሌዳዎች ፡ ላይ ፡ ተደምሯል ። በተለይም ፡ በዘመኑ ፡ የነበረውን ፡ የግእዝና ፡ ያማርኛን ፡ ውሕደትና ፡ ኅብረት ፡ እንዲሁም ፡ ችግር ፡ በመቋቋም ፡ በፊደሉ ፡ አጣጣል ፡ በድምፅ ፡ አሰጣጡና ፡ ባቀማመጡ ፡ ማለፊያ ፡ መልክ ፡ ይዞ ፡ ይገኛል ።

የአውግስጦስ ፡ ዲልማን ፡ የግእዝና ፡ያማርኛ ፡ ጥናት ፡ በዚሁ ፡ አልተገታም ። *«የኢትዮጵያ ፡ የቋንቋ ፡ ሰዋስውን ፡ ባወጣን ፡ በሰባት ፡ ዓመታችን ፡ ይህንን ፡ ትልቅ ፡ ሥራ ፡ ደግሞ ፡ ዠመርን ፡»* በማለት ፡ ይዠምራል ። የሚዠመረው ፡ ሌላው ፡ የሙያው ፡ ምስክር ፡ የኾነ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ። ይህ ፡ ትልቅ ፡ ሥራ ፡ የተባለውን ፡ የግስ ፡ መጽሐፍ ፡ አጥንቶ ፡ ተምሮ ፡ ተመራምሮ ፡ ለኅትመት ፡ ለማቅረብ ፡ ዝግጁ ፡ የኾነበት ፡ ወቅት ፡ ነበር ። *«የኢትዮጵያ ፡ መጻሕፍት ፡ ጥንታዊነትም ፡ ኾነ ፡ በታሪክ ፡ ቅርስነት ፡ እጅግ ፡ የታወቁ ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ መወሰን ፡ እጅግ ፡ ያስቸግራል ። በሥነ ፡ ጽሕፈትም ፡ በኩል ፡ ለዓለም ፡ የቋንቋ ፡ ተመራማሪዎች ፡ የሚረዱ ፡ የባህል ፡ ምንጮች ፡ ናቸው ።»* ብሎ ፡ ዲልማን ፡ ያወድሳቸዋል ።

*«አንደኛ ፡ ከኹሉ ፡ በላይ ፡ የተከበሩ ፡ መጻሕፍት ፡ ናቸው ። እነዚህም ፡ ከያይነቱ ፡ ከሚገኙት ፡ የብራና ፡ መጻሕፍት ፡ መካከል ፡ ርስ ፡ በርስ ፡ በማስተያየት ፡ ያስፈለገንን ፡ ያኽል ፡ በአውሮፓ ፡ የሚገኙትን ፡ የኢትዮጵያ ፡ መጻሕፍት ፡ ማንበብ ፡ ለጥናታችን ፡ በቂ ፡ መነሻና ፡ መረጃ ፡ አደረግን ፡»* ይልና ፡ ዲልማን ፡ ያነበባቸውና ፡ የተመለከታቸው ፡ ከመንፈሳዊ ፡ ቅርስነታቸው ፡ ጋራ ፡ የቋንቋን ፡ ብርሃን ፡ የሚያንጸባርቁ ፡ የሥነ ፡ ጽሕፈትን ፡ ኀይል ፡ የሚያጐለብቱ ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ አድንቋቸዋል ።

*«ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ብሉይም ፡ ኾነ ፡ ሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ እንዲሁም ፡ አበው ፡ ሊቃውንት ፡ ያዘጋጇቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ሊቃውንት ፡ የያሬድ ፡ ጸዋትወ ፡ ዜማና ፡ ቅኔ ፡ በሙሉ ፡ ለአሮፓ ፡ የቀለም ፡ ሰዎች ፡ እጅግ ፡ ጠቃሚዎችና ፡ ወደ ፡ ዕውቀት ፡ ጎዳና ፡ የሚመሩ ፡ ኾነው ፡ ተገኝተዋል ። በግጥምና ፡ በስድ ፡ ንባብ ፡ የተዘጋጁት ፡ እነዚህ ፡ መጻሕፍት ፡ ምትክ ፡ የማይገኝላቸው ፡ መኾኑን ፡ በጽሑፌ ፡ ላይ ፡ ገልጬዋለኹ ፡»* ይላል ፡ አውግስጦስ ፡ ዲልማን ።

*«እያንዳንዱን ፡ መጽሐፍ ፡ ስንመለከት ፡ የሚያስገርም ፡ ኹኔታ ፡ እናያለን ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡ ብራና ፡ ፍቀው ፡ ቀለም ፡ በጥብጠው ፡ መቃ ፡ ቈርጠው ፡ በጊዜው ፡ የነበሩባቸውን ፡ ችግር ፡ ኹሉ ፡ ተቋቁመው ፡ ይህን ፡ የዓለም ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ማዘጋጀታቸው ፡ በመዠመሪያ ፡ የዕውቀታቸውንና ፡ ያእምሯቸውን ፡ ስፋት ፡ ታጋሽነታቸውንና ፡ ረኃብና ፡ ጥም ፡ የማይበግራቸው ፡ መኾኑን ፡ ያሳያል ። በመጻሕፍት ፡ በቅኔና ፡ በዜማ ፡ ቤት ፡ የሚማሩት ፡ የቀለም ፡ ትምህርት ፡ ብቻ ፡ አልነበረም ። የተማሩት ፡ እንዳይረሳቸው ፡ ወቅቱ ፡ በፈቀደ ፡ መጠን ፡ የእንስሳት ፡ ቆዳን ፡ አለስልሰው ፡ ቀለም ፡ እንዲቀበል ፡ በማድረግ ፡ ወጥተው ፡ ወርደው ፡ ያስቀመጡት ፡ ቅርስ ፡ ባሕር ፡ ተሻግሮ ፡ የኤሮፕን ፡ ሊቃውንት ፡ ሊጠቅም ፡ በመቻሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡ ምስጋና ፡ ሊያገኙ ፡ ይገባል ። ከምስጋና ፡ በላይ ፡ ሌላ ፡ ቃል ፡ ካለ ፡ ለነሱ ፡ ይገባል ።»* ሲል ፡ ዲልማን ፡ ውዳሴ ፡ ሊቃውንተ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አቅርቧል ።

ዲልማን ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ሌላ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጽሑፎች ፡ ለኤሮፕ ፡ አንባብያን ፡ አቅርቧል ። የሃይማኖት ፡ ምሁር ፡ የኾነውን ፡ ያኽል ፡ በቋንቋ ፡ ጥናትና ፡ በፍልስፍናም ፡ እጅግ ፡ የተራቀቀ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ የተነሡ ፡ የቀለም ፡ ሰዎች ፡ ያቀረቧቸው ፡ ሰፋፊ ፡ ጽሑፎች ፡ መስክረዋል ። ሊቁ ፡ ዲልማን ፡ ለትውልደ ፡ ትውልድ ፡ የሚቈዩ ፡ የጥናት ፡ ጽሑፎችን ፡ ለዓለም ፡ ካተረፈ ፡ በኋላ ፡ በተወለደ ፡ በሰባ ፡ አንድ ፡ ዓመቱ ፡ እ. ፡ ኢ. ፡ አ. ፡ ባ፲፰፻፺፬ ፡ ዓ. ፡ ም. ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በሞት ፡ ተለይቷል ።

---

(ከ<u>*ዐዲስ ፡ ዘመን*</u> ፡ ሚያዝያ ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፱ ፡ ዓ. ፡ ም. ፡ የተቀዳ ።)